# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## ጉምሩክ ኮሚሽን

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION


ቁጥር/ Ref.No. 4/1798/18
ቀን/Date ጥር 12 2018

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>መመሪያ ቁጥር 1080/2017ን ለማሻሻል የወጣውን መመሪያ ቁጥር 1123/2018 ስለመላክ</u>፤

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በተሰጠው ስልጣን መሠረት "የኢትዮጵያ ጉምሩክ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 1080/2017ን ለማሻሻል መመሪያ ቁጥር 1123/2018" አውጥቷል፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያ ጉምሩክ የዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 1080/2017ን ለማሻሻል የወጣው መመሪያ ቁጥር 1123/2018 በጥብቅ ዲስፕሊን ተፈጻሚ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፤ የመመሪያውን ቅጅ 07 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሁርሳ
ኮሚሽን ኮሚሽነር

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Customs Commission No.1

<u>ግልባጭ</u>፤
- ለጉምሩክ ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ማዕከል
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>




ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia
ፖ.ሳ.ቁ. 2559

- ለዋጋ ትመናና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለአምራችና ወጪ ንግድ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባና ሥሪት አገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለህግ ተገዥነትና ሥጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለኮንትሮባንድ መከላከልና ድንበር ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለስትራቴጂክ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለስትራቴጂክ አጋርነት ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለተቋማዊ ሥጋት ሥራ አመራርና ሥነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት
- ለኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

**<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>**፣

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

**<u>በያሉበት</u>**፣

ቁጥር 1
No. 1
Documentation
Customs Commission

**የኢትዮጵያ ጉምሩክ የዋጋ አተማመን መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 1123/2018**

**Directive issued to amend the Ethiopian Customs valuation Directive number 1123/2026**

የአገራችን የጉምሩክ የዋጋ አተማመን ከአለም የንግድ ድርጅት የጉምሩክ የዋጋ አተማመን ስምምነት ጋር ለማጣጣም የወጣው መመሪያ የተወሰነ ክፍተት ስለነበረበት ክፍተቶችን በማስተካከል እንዲጣጣም ማድረግ በማስፈለጉ፤

አስመጭዎች ተጨማሪ ማስረጃ የሚያቀርቡበትን አግባብ ይበልጥ ግልፅ ማድረግ በማስፈለጉ፣

አጠቃላይ የጉምሩክ የዋጋ አተማመን ሂደቱን ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ፣

የገቢዎች ሚኒስትር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የኢትዮጵያ ጉምሩክ የዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 1080/2017 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

Whereas the directive issued to align our country's customs valuation with the World Trade Organization Customs Valuation Agreement contained certain gaps, it has become necessary to rectify these gaps to ensure compliance.; and

Whereas it has become necessary to further clarify the procedures under which importers may submit additional supporting documents; and

Whereas it is necessary to enhance the transparency of the overall customs valuation process.

Ethiopian Customs Valuation Directive No. 1080/2025 is hereby amended as follows.

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**የጉምሩክ የዋጋ አተማመን (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር 1123/2018**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**1. Short Title**

This Directive may be cited as the "**Customs Valuation (Amendment) Directive No. 1123/2025**"

**2. ማሻሻያ**

የኢትዮጵያ ጉምሩክ የዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 1080/2017 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

**2. Amendment**

The Ethiopian Customs Valuation Directive No. 1080/2025 has been amended as follows:

1/ የመመሪያው አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ (4) ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ (4) ተተክቷል፦

1. Sub-article (4) of Article 2 of the Directive is repealed and replaced by the following new sub-article (4)

2(4) **"የማነጻጸሪያ ዋጋ"** ማለት ለስጋት ስራ አመራር ብቻ እንዲያገለግል በጉምሩክ ኮሚሽን የሚደራጅ የዋጋ መረጃ ነው።

2(4) **"Reference price"** means price data compiled by the Customs Commission exclusively for use in risk management."

2/ የመመሪያው አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ (5) ተሽሯል።

2. Sub-article (5) of Article 2 of the Directive is repealed.

3/ የመመሪያው አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ (1) (2) እና (3) ተሽረው በሚከተሉት አዲስ ንኡስ አንቀጽ (1)፣(2)፤ (3)፤ ተተክተዋል። ቀጥሎም አዲስ ንዑስ አንቀፅ (4) እና (5) ተጨምረዋል።"

3. Sub-Article (1), (2), and (3) of Article 5 of the Directive are hereby repealed and replaced by the following new Sub-Articles (1), (2), and (3), and additional Sub-Articles (4) and (5) are added

1)ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ ዕቃ የግብይት ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደው ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ለተሸጠ ዕቃ በትክክል የተከፈለ ወይም ሊከፈል የሚገባ የግብይት ዋጋ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተመለከቱት ተጨማሪ ክፍያዎች ታክለውበት ይሆናል።

1. The transaction value for goods imported into the country shall be the price actually paid or payable for the goods when sold for export to Ethiopia, with the additions specified in the Proclamation and in this Directive added thereto.

2) የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጉምሩክ ኮሚሽነር ወይም በኮሚሽነሩ በየደረጃው ሃላፊነት የተሰጠው የጉምሩክ ሹም፤ የሰነድ መርማሪ ወይም የዋጋ ትመና ባለሙያ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ያቀረበውን ዋጋ በቀጥታ ሳይቀበል ዲክላራሲዮን አቅራቢው ተጨማሪ መረጃዎች እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፦

2. Where any of the following circumstances arise, the Customs Commissioner, or a customs officer authorized by the Commissioner at the appropriate level, a document examiner, or a valuation expert may request the declarant to provide additional information without directly accepting the value submitted by the

declarant.

ሀ) በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የግብይት ዋጋ ወይም ደጋፊ ሰነዶች ያልተሟሉ ሆነው ሲገኙ፤

a) Where the transaction value declared by the declarant or the supporting documents provided are incomplete;

ለ) በአዋጁ አንቀጽ 90 (1) ከ (ሀ) እስከ (ሠ) የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ያልተሟሉ ሆኖ ሲገኝ፤

b) Where any of the circumstances set out in sub-articles (a) to (s) of Article 90(1) of the Proclamation are not fulfilled;

ሐ) የእቃው መገለጫ (ብዛት፤ አይነት፤ ጥራት፤ መለኪያ፤ የስሪት አገር፤ የተመረተበት ቀን) ወይም ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች ወይም ማስረጃዎች በትክክል ያልተገለጹ ወይም ያልተሟሉ ሆኖ ሲገኝ፤

c) Where the description of the goods (including quantity, type, quality, specifications, country of origin, and date of production) or any other required information or supporting evidence is inaccurately declared or incomplete;

መ) ኮሚሽኑ የሃሰት ወይም የተጭበረበረ ማስረጃ የቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ያለው ከሆነ፤

d) Where the Commission possesses evidence that false or forged documents/evidence have been presented;

ሠ) በእቃው የግብይት ዋጋ ውስጥ በጉምሩክ አዋጁ አንቀጽ 96 የተመለከቱት ተጨማሪ ወጪዎች ያልተካተቱ ወይም ሊረጋገጥ የሚችል ማስረጃ ያልቀረበ ከሆነ፤

e) Where the additions provided for under Article 96 of the Customs Proclamation have not been included in the transaction value of the goods, or where the declarant has failed to submit verifiable evidence thereof;

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚከተሉት እርምጃዎች እንደቅደም ተከተላቸው ይወሰዳሉ፦

3. When any of the situations listed in sub-article (2) of this Article arise, the following measures shall be implemented in sequential order:

ሀ) ኮሚሽነሩ ወይም በኮሚሽነሩ በየደረጃው ሃላፊነት የተሰጠው የጉምሩክ ሹም፤ የጉምሩክ ሰነድ ምርመራ ባለሙያው ወይም የጉምሩክ የዋጋ ትመና ባለሙያው በበቂ የህግ ምክንያት ላይ በመመስረት፤ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በአካል በመቅረብ ማብራሪያ እንዲሰጥ ወይም የቀረበው የእቃ ዋጋ ትክክለኛ መሆኑን የሚያረጋግጡ ተጨማሪ ማስረጃዎችን በ15

a) The Customs Commissioner, or any customs officer authorized by the Commissioner at the relevant level, a document examiner, or a valuation expert may, based on reasonable grounds provided for by law, request the declarant to appear in person to give explanations or to

ቁጥር 1
No. 1
Documentation
Customs Commission

ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ይጠይቃል።

submit additional supporting evidence verifying the correctness of the declared goods value within 15 days.

ለ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተገለጸው ሁኔታ ሲያጋጥም በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የግብይት ዋጋ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው ዋጋ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ካለው የዋጋ ለውጥ ጋር የተጣጣመ ወይም በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው ዋጋ ትክክለኛ ሆኖ ሲገኝ ወይም በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ሲታይ በዲክላራሲዮን አቅራቢው ያቀረበው ዋጋ ትክክለኛው የአምራቹ ዋጋ ሆኖ ሲገኝ ነው። ኮሚሽነሩ ወይም በኮሚሽነሩ በየደረጃው ሃላፊነት የተሰጠው የጉምሩክ ሹም ወይም የጉምሩክ ሰነድ መርማሪ ወይም የጉምሩክ የዋጋ ትመና ባለሙያ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበውን ትክክለኛ ዋጋ በመቀበል የዲክላራሲዮኑ ሂደት እንዲቀጥል ማድረግ አለበት።

b) In the event that the situation specified in this sub-article, paragraph (a) of this Article arises, the transaction value presented by the declarant shall be acceptable only where the declared price conforms to internationally recognized price variations, or where the declared price is determined to be correct, or where objective and quantifiable evidence demonstrates that the price submitted by the declarant corresponds to the true manufacturer's price. The Customs Commissioner or any customs officer authorized by the Commissioner at the relevant level, document examiner, or valuation expert shall, upon acceptance of the accurate value declared by the declarant, permit the processing of the declaration to continue.

ሐ) ዲክላራሲዮን አቅራቢው በዚህ ንኡስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተጠየቀውን ትክክለኛውን የግብይት ዋጋ ማረጋገጥ የሚያስችል ማስረጃ ወይም የአምራቹን ዋጋ ያላቀረበ እንደሆነ፤ ኮሚሽነሩ ወይም በኮሚሽነሩ በየደረጃው ሃላፊነት የተሰጠው የጉምሩክ ሹም፤ የጉምሩክ ሰነድ መርማሪ ወይም በየደረጃው ኃላፊነት የተሰጠው የጉምሩክ የዋጋ ትመና ባለሙያ ህጋዊ ውሳኔውን ለአስመጪው በማሳወቅ እና ሊከፈል የሚገባውን የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ መወሰን አለበት።

c) If the declarant does not, within the period specified under paragraph (a) of this sub-article, provide evidence sufficient to verify the correctness of the transaction value or the manufacturer's price, the Customs Commissioner, or any customs officer authorized by the Commissioner at the relevant level, document examiner, or valuation expert authorized at the appropriate level shall inform the importer of the decision taken in accordance with the law and shall proceed to assess the customs duty and taxes due.

4) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚጠየቀው ተጨማሪ ማስረጃ በምርመራ ላይ ካለው ጉዳይ

4. Any additional evidence requested pursuant to this Article shall be

ጋር በቀጥታ የሚገናኝ እና ዲክላራሲዮን አቅራቢው በመደበኛ የንግድ አሰራር ሊያገኘው በሚችለው ማስረጃ ላይ የተወሰነ መሆን አለበት::
"ከላይ የተጠቀሰው ገደብ ቢኖርም፣ የግዢ ወይም የሽያጭ ውል፣ ደረሰኝ፣ የክፍያ ሰነድ፣ የትራንስፖርት ሰነድ እና ሌሎችም የንግድ መረጃ ልውውጥ የተደረገባቸው ሰነዶች ማካተት ይኖርበታል::"

restricted to evidence directly relevant to the transaction under review and which the declarant is reasonably able to obtain in the normal course of trade. Notwithstanding the foregoing limitation, such evidence shall include purchase or sales contracts, invoices, payment documents, transport documents, and any other documents containing exchanged commercial information.

5) ዲክላራሲዮን አቅራቢው የአምራቹን የዋጋ ዝርዝር፣ የገበያ ትንተና ወይም ከጉዳዩ ግንኙነት የሌላቸውን የንግድ መረጃዎች እና የመሳሰሉትን መረጃዎች ማቅረብ ያለመቻሉ ያቀረበው የእቃው የግብይት ዋጋ ውድቅ እንዲደረግ ምክንያት ሊሆን አይችልም::

5. The fact that the declarant is unable to provide the manufacturer's price list, market analyses, commercial information that has no connection with the transaction in question, or similar data shall not be a reason for rejecting the transaction value of the goods submitted by the declarant.

4/ የመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሽሮ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ አንቀጽ 2 ተተክቷል፦

4. Article 6 sub article 2 of the Directive is hereby repealed and substituted with the following new sub article Article 2:

2) የዋጋ ትመናን ልማት ዳይሬክቶሬት በዚሁ መሰረት የቀረበለትን ጉዳይ በመመርመር ከዚህ አንቀጽ ጋር በተጣጣመ አኳኋን እንዲፈጸም መመሪያ የመስጠት እና እቃዎቹ እንዲለቀቁ ለማድረግ ተገቢ ያልሆነ የዋስትና ጥያቄ እንዳይቀርብ ማድረግ የሚያስችል እርምጃ መውሰድ አለበት::

2. The Valuation and Development Directorate shall, after investigating the matter referred to it accordingly, take the necessary steps to provide guidance for the implementation of the procedure in conformity with this Article and to ensure the release of the goods without the imposition of an inappropriate security requirement.

5/ "የመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ "ለ" ተሽሮ በአዲስ ፊደል ተራ "ለ" ተተክቷል::

5. Sub-article (2), paragraph (b) of Article 7 of the Directive is hereby repealed and substituted with the

ቁጥር 1
No. 1
Recordes Documentation
Ethiopia customs commission

following new paragragh (b):

ለ/ በዲክላራሲዮን አቅራቢው በተመሳሳይ ወቅት ግንኙነት ለሌላቸው ገዢዎች የተሸጠ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃ የግብይት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በማነፃፀሪያ የዋጋ መረጃ ውስጥ ከሚገኝ የአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ ጋር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ወይም በአንቀጽ 5(3)/ለ/ መሰረት ተቀባይነት ካገኘ፤

b) Where a comparison shows that the declared price is identical or very close to the transaction value of identical or similar goods sold by the declarant to buyers with no relationship during the same time period, or to the price of identical or similar goods appearing in the comparative price database; or where the price has been accepted in accordance with sub-article (3)(b) of Article 5;

6/ የመመሪያው አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 4 ተሽሯል።

6. Article 10(4) of the directive is hereby repealed.

7/ የመመሪያው አንቀድ 17 ንኡስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ (2) ተተክቷል።

7. Sub-article (2) of Article 17 of the Directive is hereby repealed and substituted with the following new sub-article (2):

(2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚይዘውን መረጃ የሚጠቀምበት የስጋት ስራ አመራርን ለመደገፍ እና የጉምሩክ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ግብይቶች ለመለየት ይሆናል።"

(2). The data specified in sub-article (1) of this Article shall be utilized exclusively for the purpose of supporting risk management and for selecting transactions for customs control.

8/ የመመሪያው አንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ 4 ተሽሯል፤

8. Sub-article (4) of Article 18 of the Directive is hereby repealed;

9/ የመመሪያው አንቀጽ 19 ተሽሯል።

9. Article 19 of the Directive is hereby repealed.

10/ "የመመሪያው አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ (14) ፊደል ተራ (ሰ) ተሽሯል። ፡ እንዲሁም የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 15 ተጨምሯል።

10. Paragraph (s) of sub-article (14) of Article 23 of the Directive is hereby repealed. In addition, the following new sub article 15 is added.

(15) ኮሚሽኑ ዲክላራሲዮን አቅራቢው ተጨማሪ መረጃ ወይም ሰነድ እንዲያቀርብ ለመጠየቅ የሚችለው ዲክላራሲዮን ከቀረበበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ እና በዲክላራሲዮን

(15) Any request by the Commission for the declarant to provide additional information or documents shall be limited to matters related to the

ቁጥር 1
No. 1
...Documentation
...Customs Commission

አቅራቢው ላይ ተገቢ ያልሆነ እና ከልክ ያለፈ ግዴታን በማያስከትል ሁኔታ መሆን አለበት።

1.1/ የመመሪያው አንቀጽ 34 ንኡስ አንቀጽ 3 ተሽሯል።

## 3. መመሪያው የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በገቢዎች ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ ጥር 2018 ዓ.ም

አይናለም ንጉሴ

የገቢዎች ሚኒስትር

declaration in question and shall not place an undue or disproportionate obligation on the declarant.

11. Sub-article (3) of Article 34 of the Directive is hereby repealed.

## 3. Effective Date of the Directive

This Directive shall enter into force as of the date of its Registration by the Ministry of Justice and posted on the official website of the Ministry of Revenues.

**Addis Ababa, January, 2026**

**Aynalem Nigussie,**

**Minister of Revenues**